Queensland Positive People
INCLUSIVE, INNOVATIVE HIV SERVICES

ashm
Australasian Society for HIV, Viral Hepatitis and Sexual Health Medicine

# ለመዲኬር ብቃት አለማግኘት

## እ ው ነ ታ ጽ ሁ ፋ ዊ ወ ረ ቀ ት

**በኲዊንስላንድ ውስጥ እንዴት ለኤችአይቪ/HIV መዲኬር እና ህክምና መጠቀም እንደሚቻል**

ከኤችአይቪ/HIV ጋር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ተከታታይ የሆነ መማክርት/ቀጠሮዎች ከሙያ ልምድ ያለው ሀኪም ጋር በማቀናጀት ለኤችአይቪ/HIV ቁጥጥርና ክትትል ማድረጉ የእነሱ ጤና እንክብካቤ ቡድን እንደ አንዱ አካል ይሆናል። የርስዎ ሀኪም ሁልጊዜ እንደሚያይዎት እና አስፈላጊ ለሆኑ የደም ምርመራ (የበሽታ ጥናት ምርመራ) በማቀናጀት የርስዎን ህክምናና ጤና በመቆጣጠር ሲያነጋግርዎት የመድሃኒት ማዘዣ (አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ) ይሰጥዎታል።

የመዲኬር ካርድ የሚሰጠው ለአውስትራሊያ ዜጋዎች፣ ለቋሚ መኖሪያ ፈቃድ ላላቸው ነዋሪዎች (ወይም ለቋሚ መኖሪያ ፈቃድ ቪዛ ላመለከቱ) እና በአውስትራሊያ ውስጥ ለሚኖሩ የኒውዚላንድ ዜቾች ይሆናል። . በመዲኬር በኩል ያለክፍያ በነጻ ህዝባዊ የጤና ጥበቃ እንክብካቤ ሲቀርብ፣ ወይም በግል ጤና ጥበቃ እንክብካቤ ላገኙ ቡድኖች የወጪ ማካካሻ ይቀርብላቸዋል።

### በኲዊንስላንድ ውስጥ ለኤቻይቪ/HIV ህክምና እንክብካቤ የመጠቀም ምርጫዎች

በቅርቡ እንዳለው የታወቀበት ሰው ቀደም ብሎ ከኤችአይቪ እንክብካቤ ሰጪ ጋር መገናኘቱ ጠቃሚ ነው። መዲኬር ለመጠቀም ካልቻሉ (የመዲኬር ፈቃድ ላለማግኘት/MI)፣ ከዚህ በታች ባሉት የመተላለፊያ ዘዴዎች አድርጎ ለህክምና እንክብካቤ መጠቀም ይችላሉ

**1) መዲኬር የለም/ ቢጋራ ጤና ጥበቃ እንክብካቤ ስምምነት የለም/ የግል ዋስትና ኢንሹራንስ የለም**
**2) መዲኬር የለም/ ቢጋራ ጤና ጥበቃ እንክብካቤ ስምምነት የለም/ የግል ዋስትና ኢንሹራንስ**
**3) መዲኬር የለም/ ቢጋራ ጤና ጥበቃ እንክብካቤ ስምምነት**

### 1) መዲኬር የለም/ ቢጋራ ጤና ጥበቃ እንክብካቤ ስምምነት የለም/ የግል ዋስትና ኢንሹራንስ የለም

ለርስዎ የኤችአይቪ እንክብካቤ ሀኪም ለማየት፣ የህክምና ቀጠሮን በኲዊንስላንድ የመንግሥት ኤችአይቪ/ወሲባዊ ጤና ጥበቃ አገልግሎት በኩል ማቀናጀት ይቻላል። **ከነዚህ አገልግሎቶች ውስጥ በአንደኛው ላይ ከሄዱ በአጠቃላይ ክፍያ እንደሌለ ነው።**

በሚከተለው ድህረገጽ ላይ ስለ ኲዊንስላንድ የመንግሥት ኤችአይቪ/ወሲባዊ ጤና ጥበቃ አገልግሎት ዝርዝር አድራሻና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች ይቀርባል።

*ለኲዊንስላንድ ጤና ጥበቃ በድህረገጽ*
*http://tinyurl.com/qrhtx46 ላይ መጎብኘት*

በአማራጭነት ደግሞ ሙሉውን ለመክፈል አቅም ካለዎት የግል ኤችአይቪ ተቆጣጣሪ ህክምና ባለሙያን (S100 ዶላር ለአጠቃላይ ሀኪም / S100 GP) በመክፈል ማየት ይችላሉ። ምርጫው የርስዎ ነው። በመንግሥት የኤችአይቪ/ወሲባዊ ጤና ጥበቃ አገልግሎት መስጫ ለመሄድ አይኖርብዎትም።

የኤችአይቪ ተቆጣጣሪ ሀኪም (የግል ወይም የመንግሥት ሀኪም), የት እንደሚገኝ እርግጠኛ ካልሆኑ እባክዎ በአካባቢዎ ያለን የኤችአይቪ ሀኪም ለማግኘት በድህረገጽ https://www.ashm.org.au/prescriber-locator/ ላይ ገብቶ ማየት።

የርስዎን ቀጠሮ በሚያቀናጁበት ጊዜ በርስዎ ሀኪም ለሚደረግልዎ መማክርት ምን ያህል እንደሚከፈል መጠየቅ እንደሚያስፈልግ በጥብቅ ይመከራሉ። በግላዊ የህክምና ክፍያዎች ከ AUD $80 እስከ $200 ዶላር ሊለያይ ሲችል ይህም እንደ የርስዎ መማክርት የሚወስደው ጊዜ ወይም አወሳሳቢነት ይወሰናል። እንዲሁም ከመማክርት ክፍያ በተጨማሪ ለበሽታ ምርመራ/ደም ምርመራዎም ምን ያህል እንደሚከፈል ግምት ውስጥ ማስገባት አለብዎት።

### 2) መዲኬር የለም/ ቢጋራ ጤና ጥበቃ እንክብካቤ ስምምነት የለም/ የግል ዋስትና ኢንሹራንስ

የመዲኬር እንክብካቤን እንደ አንደኛው መንገድ/pathway 1) ለመጠቀም ተመሳሳይ የሆነ ምርጫ አለዎት፣ ይሁን እንጂ በ S100 ዶላር ግላዊ የአጠቃላይ ሀኪምን/ GP ለማየት ከመረጡ ለርስዎ በሚደረግ መማክርትና የደም ምርመራ ክፍያዎች ላይ በከፊሉ የሚሸፍኑ አንዳንድ የዋስትና ኢንሹራንስ ፖሊሲዎች አሉ። በርስዎ ሀኪም ከሚጠየቅ ክፍያ ውስጥ ምን ያህል እንደሚመለስ ከርስዎ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር ጠይቆ ማጣራት አለብዎ። በአጠቃላይ ሙሉ የክፍያ መጠን መክፈል አለብዎት፣ ከዚያ በኋላ ለኢንሹራንስ ኩባንያ እንዲመለስልዎት መጠየቅ።

እንዲሁም አንዳንድ ኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ለሚያካሂዱት የደም ምርመራ ወጪዎች በከፊሉ ወይም በሙሉ ክፍያ ስለሚሸፍኑ፣ እባክዎ የዚህ ዓይነት ቅንጅት ካላቸውና የትኛው የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ስለመሆናቸው ከበሽታ ጥናት ምርመራ ኩባንያ ጋር ማጣራት።

***ማስታወሻ/NB: ለእረፍት አውስትራሊያ ውስጥ ከሆኑ የግላዊ ኢንሹራንስም ለጉዞ ዋስትና ኢንሹራንስ ያካትታል።***

### 3) መዲኬር የለም/ ቢጋራ ጤና ጥበቃ እንክብካቤ ስምምነት

ከበልጂም፣ ከፊንላንድ፣ ከጣሊያን (በጣሊያን አገር ውስጥ መኖር ላይኖርብዎት ይችላል፣ ነገር ግን የጣሊያን ዜጋ መሆን እንዳለብዎትና ሌሎችን የስምምነት ሁኔታዎች ማሟላት አለብዎ)፣ ከማልታ፣ ከነዘርላንድስ፣ ከኒውዚላንድ፣ ከኖርዋይ፣ ከአይረላንድ፣ ከስሎቬኒያ፣ ከስወደን እና ከናይትድ ኪንግዶም ጋር የአውስትራሊያ መንግሥት ቢጋራ የጤና ጥበቃ ስምምነት አለው።

በስምምነቱ ላይ የሚካተት አስፈላጊ ለሆኑ የህክምና እንክብካቤ ነው። በዚህ መካተት ያለበት:

1. ሲታመሙ ወይም ጉዳት ሲደርስ ወደ አገርዎ እስኪመለሱ ድረስ መቆየት ካልቻሉ እንክብካቤን
2. በመዲኬር የሚካተት እንክብካቤን፣ እና
3. ያለውን የስምምነት ሁኔታዎች ማሟላት አለብዎ።

እርስዎ ከኒውዚላንድ ወይም ከረፑብሊች አይረላንድ ከሆኑ በዚህ የሚካተተው:

Queensland Positive People
INCLUSIVE, INNOVATIVE HIV SERVICES

ashm
Australasian Society for HIV, Viral Hepatitis and Sexual Health Medicine

1. በመንግሥት ሆስፒታል ውስጥ እንደ ህዝባዊ ታካሚ ሆኖ አስፈላጊ የህክምና እንክብካቤ
2. በዝቅተኛ ዋጋ ለመድሃኒት ማዘዣ ወረቀት - ይህ በፋርማሲ ጥቅሞች አሰራር (PBS) ላይ በተመዘገበው መድሃኒቶች መሰረት አጠቃላይ የክፍያ ዋጋ

እርስዎ ከዚህ ውጭ በሌላ አገራት ስምምነት ላይ ከሆኑ በዚህ የሚካተተው:

1. ከሆስፒታል ውጭ አስፈላጊ የህክምና እንክብካቤ
2. በመንግሥት ሆስፒታል ውስጥ እንደ ህዝባዊ ታካሚ ሆኖ አስፈላጊ የህክምና እንክብካቤ
3. በዝቅተኛ ዋጋ ለመድሃኒት ማዘዣ ወረቀት - ይህ በፋርማሲ ጥቅሞች አሰራር (PBS) ላይ በተመዘገበው መድሃኒቶች መሰረት አጠቃላይ የክፍያ ዋጋ

ከሚከተለው አገር ተማሪ ከሆኑ በዚህ ላይ አይካተቱም:

1. ፊንላንድ/Finland
2. ማልታ/Malta
3. ኖርዌይ/Norway
4. የሪፑብሊክ አይረላንድ/the Republic of Ireland

በተማሪ ቪዛ ወደ አውስትራሊያ ለመምጣት የሚፈልጉ አብዛኞች ለውጭ አገር ተማሪ የጤና ጥበቃ እንዲካተት ይፈልጋሉ።

በአውስትራሊያና በርስዎ አገር መካከል ስላለው ተግባራዊ የጋራ ጤና ጥበቃ እንክብካቤ ስምምነት በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፤ እባክዎ ከህክምና ቢሮ ምክር መጠየቅ።

**የበለጠ መረጃ ለማግኘት የሰብ አዊ አገልግሎት መምሪያን በድህረገጽ: http://tinyurl.com/lrm6gea ላይ መጎብኘት።**

## ያለኝን የኤችአይቪ/ HIV ሁኔታ መረጃ ሀኪሞች ለአገር ጉዳይ መምሪያ (DHA) አውጥተው መስጠት ይኖርባቸዋልን?

የለባቸውም፤ በመንግሥት የኤችአይቪ/ HIV ሀኪሞችም ሆኑ በህዝባዊ HIV/ወሲባዊ ጤና ጥበቃ አገልግሎት እና በግላዊ ሙያተኛ በኩል መረጃዎችን አውጥቶ ለአገር ጉዳይ መምሪያ (DHA) መስጠት አያስፈልግም። በአውስትራሊያ ውስጥ የኤችአይቪ/ HIV እንዳለብዎት ከታወቀ ባለዎት ቪዛ ላይ ችግር አይፈጥርም። ያለዎትን ቪዛ ለማራዘም ወይም ለሌላ ቪዛ ማመልከት ከፈለጉ፤ እባክዎ ከአውስትራሊያ የተመዘገበ የመጤ ማይግሬሽን ድርጅት ምክር ማግኘት።

## በኩዊስላንድ ውስጥ ለኤችአይቪ/HIV ህክምና (መድሃኒት) ስለመጠቀም

በአውስትራሊያ ውስጥ ለኤችአይቪ/HIV እና ለሌሎች የመድሃኒት ማዘዣዎች በአውስትራሊያ *የፋርማሲ ጥቅሞች አሰራር(PBS) በኩል ይገኛል* – ይህም ለአውስትራሊያ መዲኬር ካርድ ላላቸው ብቻ የዋጋ ቅናሽ (አነስተኛ ክፍያ) ይቀርባል። የዋጋ ቅናሽ ለሚደረግለት የPBS መድሃኒቶች የመዲኬር ካርዶች ለሌላቸው ሰዎች አይቀርብም።

በዚህ ሳቢያ የውጭ አገር ጎብኝዎች (በአውስትራሊያ ውስጥ ለሚሰሩ፤ ለሚማሩ ወይም ለእረፍት ላሉት) የመዲኬር ካርድ ማግኘት ስለማይፈቀድላቸው በጋራ ጤና ጥበቃ እንክብካቤ ስምምነት ውስጥ ስለማይካተቱ ታዲያ ለኤችአይቪ/HIV ህክምናዎችን ለማግኘት ሌላ አማራጮችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይሆናል።

***ማስታወሻ: የግላዊ (S100 HIV መድሃኒት አዛዦች) በተለይ ሁኔታ የሰለጠኑና በኤችአይቪ/HIV ህክምና ለመድሃኒት ማዘዣ የመጻፍ ስልጣን አላቸው። አጠቃላይ ሀኪም (GP) ለየት ያለ ስልጠና ስለሌለው ለኤችአይቪ መድሃኒት ማዘዣ ወረቀት መጻፍ አይችልም።***

## በኩዊንስላንድ ውስጥ ለኤችአይቪ/HIV መድሃኒት ስለማግኘት ምርጫዎች

**1) ግላዊ (የግል ኢንሹራንስ)**
**2) በግለሰብ ወደ አገር የማስገባት አሰራር**
**3) ሁሉን ለሚያካትት መድሃኒቶች**
   **a) ፋርማሲዎች**
   **b) በመስመር ላይ**
**4) ክሊኒካል ሙከራዎች**
**5) ርህራሄ ባለው አቅርቦት**
**6) ለድንገተኛ ችግር የገንዘብ እርዳታ**

### 1) የግል ኢንሹራንስ

ለመዲኬር/Medicare/PBS አቅርቦት የማያገኙ ከሆን ግን የግል ኢንሹራንስ ካለዎት፤ ከፋርማሲ ለገዙት የኤችአይቪ/HIV መድሃኒት ወጪ መጠየቅ ይችሉ ይሆናል። መጠየቅ የሚችሉት የገንዘብ መጠን እንደ ያለዎት የኢንሹራንስ ኩባንያና ፖሊሲ መሰረት መጠኑ ይወሰናል። ከንግድ ምልክት ካላባቸው መድሃኒቶች ባሻገር ለአጠቃላይ መድሃኒቶች (ከዚህ በታች ያለን ማየት) እንዲቀርብ ጽሁፋዊ ፈቃድ ካለዎት ዋጋው ረከስ ያለ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ጉዳይ የርስዎን ኤችአይቪ/HIV ሀኪም ማነጋገር።

### 2) በግለሰብ ወደ አገር የማስገባት አሰራር

ከትውልድ አገርዎ መድሃኒቶችን ማስመጣት ዋጋው ረከስ ያለ ሊሆን ይችላል። በግለሰብ ወደ አገር የማስገባት አሰራር ዘዴ መሰረት ለግለሰብ የህክምና እቃዎችን በህጋዊ መልኩ ከሌላ አገር ግለሰቡ ማስገባት ይቻላል።

በግላዊ ከውጭ አገር ማስገባት የሚፈጠር:

a. ግለሰቡ በአውስትራሊያ ውስጥ ሆኖ የህክምና እቃዎች ከውጭ አገር ያለ አቅራቢ ወይም ቤተሰብ/ጓደኛ እንዲላክላቸው ካደረጉ፤ እና
b. እቃዎቹን የሚጠቀም ግለሰቡ ወይም የቅርብ ዘመድ አባል እንደሆነ ታዲያ እቃዎችን ለሌላ አቅራቢ ወይም ለማንም ሰው አይሸጥም።

በግልዎ የሚጠቀሙበትን መድሃኒቶች ከውጭ አገር (ከትውልድ አገርዎ) ለማስመጣት በህጋዊ ይፈቀድልዎታል – **በዚህን ጊዜ ለሶስት (3) ወራት አቅርቦት** – በአውስትራሊያ ጤና ጥበቃ መምሪያ (የህክምና እቃዎች አስተዳደር – TGA) መመሪያ መሰረት ይሆናል ድህረገጽ: *www.tga.gov.au/personal-importation-scheme*

ይህ ማለት አውስትራሊያ ውስጥ እየኖሩ ለኤችአይቪ/HIV ህክምና የሚሆን ከትውልድ አገርዎ ማስገባት ይችላሉ። በትውልድ አገርዎ ያለው ኤችአይቪ/HIV ሀኪም ከአውስትራሊያ ውስጥ ካለው የኤችአይቪ/HIV ሀኪምዎ ጋር መነጋገር ያስፈልግ ይሆናል።

### 3) ሁሉን ለሚያካትት መድሃኒቶች

ሁሉን የሚያካትት መድሃኒቶች በተለያዩ ፋክተሪዎች የሚመረት በበለጠ አቅም መቀረብ የሚችል ሲሆን ነገር ግን ከዋናው ፋክተሪ ማምረቻ የንግድ ምልክት ካላቸው መድሃኒቶች ጋር ሲነጻጸር አሁንም እኩል ውጤት ይኖራቸዋል። ሁሉን የሚያካትት መድሃኒቶች እንዲሁም የንግድ ምልክት ስም ያለው መድሃኒት ይሰራል፤ ምክንያቱም ተመሳሳይ የመድሃኒት ስራ ስላላቸው ነው። ሁሉን ያካተተ የኤችአይቪ/HIV መድሃኒቶች ከዋጋ ቅናሽ/ PBS ኤችአይቪ/HIV መድሃኒቶች ጋር ሲነጻጸር በበለጠ ውድ እንደሆነ፤ እነዚህም ከንግድ ምልክት ስም ካለው መድሃኒት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ወጪን ቆጣቢዎች ናቸው።

**a. ፋርማሲዎች**

Queensland Positive People
INCLUSIVE, INNOVATIVE HIV SERVICES

ashm
Australasian Society for HIV, Viral Hepatitis and Sexual Health Medicine

አንዳንድ ሁሉን ያካተተ በንግድ ምልክት ስም የተሰየሙ መድሃኒቶች በአውስትራሊያ ፋርማሲዎች በኩል ይቀርባል። በሁሉም ያካተተ ስያሜ ለሚቀርብ፤ እርስዎ የተለያዩ ስያሜ ያቀፈ መድሃኒቶችን የሚወስዱ ከሆነ፤ ከርስዎ የኤችአይቪ/HIV ሀኪም በሚሰጥዎት የግላዊ መድሃኒት ማዘዣ ወረቀት መግዛት ይችላሉ።

**b. በመስመር ላይ**

ለኤችአይቪ/HIV ሁሉን ያካተተ መድሃኒቶችን በመስመር ላይ ማዘዝ ሲቻል እንዲሁም በግለሰብ ከሌላ አገር ማስመጣት አሰራር ዘዴ (ከዚህ በላይ ያለን ማየት) ማስመጣት ይህም የመዲኬር/PBS ለሌላቸው ሰዎች አቅም እንዲያገኙ እንደ አማራጭ ሊሆን ይችላል።

### *ሁሉን ያካተተ መድሃኒት መውሰዱ ደህንነትና አስተማማኝነት አለውን?*

ስለ ሁሉን ያካተተ የኤችአይቪ/HIV መድሃኒት ደህንነትና አስተማማኝነት በዓለም አቀፍ ጤና ጥበቃ ድርጅት (WHO) የተረጋገጠ ነው።

በመስመር ላይ የርስዎ አቅራቢ በ WHO ፈቃድ ያገኙ ሁሉን ያካተተ መድሃኒቶች ዝርዝር ስለሚኖር ታዲያ እንደ ንግድ ስም ያለው (ዋና ማንፋክተሪ ማምረቻ) መድሃኒቶች ጥሩ ውጤት እንደሚያመጣና የርስዎን ኤችአይቪ/HIV ለማከም እርግጠኛ ይሆናሉ።

### *ምን ዓይነት ሁሉን ያካተተ መድሃኒቶች ይቀርባሉ?*

በአሁን ጊዜ የሚቀርቡት የንግድ ስም ያላቸው ኤችአይቪ/HIV መድሃኒቶች ሁሉም ሁሉንም ባካተተ መድሃኒት መልኩ ይቀርባል። የርስዎ ኤችአይቪ/HIV ሀኪም ይህንን ሊከሰትብዎ የሚችልን ያጣራል።

### *ሁሉን ያካተተ መድሃኒቶችን ማዘዝ እና ስለማስጫን*

*በመስመር ላይ ብዙ የተለያዩ ፋርማሲዎች አሉ። ከዚህ ነታች የተዘረዘረው በጣም ያደክማል ማለት አይደለም ነገር ግን ለሁሉም ያካተተ መድሃኒቶች ለመግዛት ምርጫዎችን ለመፈላለግ እንዲጀምሩ ይረዳል:*

- *a. www.aids-drugs-online.com*
- *b. www.alldaychemist.com*
- *c. www.inhousepharmacy.vu*

የኤችአይቪ/HIV መድሃኒቶች ዋጋ ከቦታ ወደ ቦታ በጣም ሊለያይ ስለሚችል ታዲያ ክፍያዎችን ለማወዳደር ከአንድ በላይ በመስመር ላይ ባሉት ሁሉን ያካተተ የመድሃኒት አቅራቢ ኩባንያ ድህረገጽ እንዲያዩ ይመረጣል።. እንዲሁም በመስመር ላይ ማዘዣ ኩባንያዎች የሚሸጡት በ US$ ዶላር ስለመሆኑ ማወቅ ስለዚህ በማንኛውም የገንዘብ ልውውጥ መለወጥ በመድሃኒቶችን ዋጋ ላይ ከቀን ወደ ቀን መጠነኛ ችግር ሊፈጥር ይችላል። በተደጋጋሚ በመስመር ላይ ትእዛዝ ባቀረቡበት ኩባንያዎች ስላቀረቡት ትእዛዝ በሚገባ ግባባት ስለሚቻል በዚያ ቢቀጥሉ ይመከራል።

**ትእዛዝ ከማካሄድዎ በፊት** ከርስዎ ህክምና ጋር የሚመጣጠንን ትክከለኛውን የንግድ ምልክት ብራንድ ወይም ሁሉን ያካተተ የመድሃኒት ስሞችን (እና ጥንካሬ) ከርስዎ የኤችአይቪ/HIV ክሊኒክ ጋር ማጣራት አለብዎት። የርስዎን ትእዛዝ በሚያቀርቡበት ጊዜ ለሚከሰት የመድሃኒት ጥያቄ ስህተት እንዳይፈጠር ለማረጋገጥ ይህ እንደሚረዳ ነው፡

ለማዘዝ የመድሃኒት ማዘዣ ወረቀት ማቅረብ አለብዎ፤ ይህም በአውስትራሊያ ለኤችአይቪ/HIV ሀኪም (እንዲሁም ለርስዎ ኤችአይቪ/HIV ህክምና እንክብካቤ ተቆጣጣሪ) በማመካከር ማግኘት ይቻላል።

በድህረገጽ ሞተር ላይ የሚያዙትን ሲፈላልጉ ታዲያ መድሃኒቱ ካለ በመድሃኒት ማዘዣ ላይ የተመዘገበን ወይም የፈለጉትን መድሃኒት/ቶች **በንግድ ምልክት ስም ብራንድ** ላይ ወይም በ**ሁሉን ያካተተ (እንዳማራጭ) መድሃኒት ስም** ላይ መጻፍ እንደሚችሉ ነው።

**የርስዎን ትእዛዝ በሚያቀርቡበት ጊዜ** ስካን ማድረግ እንደሚያስፈልግና የርስዎን ትእዛዝ ካለዎት የመድሃኒት ማዘዣ ወረቀት ጋር ማስገባት። የርስዎ መድሃኒት ማዘዣ ወረቀት ለአቅራቢው (የመድሃኒት ስም በማሳየት) ጠቃሚ መመሪያን ሲያቀርብ ይህም ከመድሃኒት ማዘዝ ጋር በተዛመደ ስህተቶች እንዳይፈጸም እርግየኛ እንዲሆኑ ይረዳል እንዲሁም ለርስዎ ሁሉን ያካተተ ህክምና አዘጋጅቶ ለመስጠት ስልጣን እንደሰጡ ይረዳል።

ለማድረስ የመርከብ ጉዞ ጊዜ  ሊለያይ ይችላል። ስለነርሱ የመርከብ ጉዞ ጊዜ እንዲሁም ለመርከብ ማጓጓዣ ክፍያዎች (ካለ) ለመረጡት የመስመር ላይ ኩባንያ መጠየቁ ጠቃሚ ነው። የመድሃኒት አቅርቦት ከማለቁ በፊት ከ1 እስከ 2 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ ማዘዙ ይመከራል።

በርስዎ የአካባቢ መድሃኒት ማዘዣ ላይ ላልተጻፈ ማንኛውንም መድሃኒቶች አይዘዙ።

### 4) ክሊኒካል ሙከራዎች

እርስዎ መሳተፍ ሊፈቀድልዎ የሚችል **በክሊኒካል ሙከራ** ስለመቅረብ መኖሩን ለርስዎ ሀኪም መጠየቅ ይችሉ ይሆናል። ይህ ሙከራ በሚደረግበት ጊዜ እርስዎ ያለክፍያ በነጻ የጤና ጥበቃ እንክብካቤና ህክምና ለመጠቀም ያስችልዎታል። በክሊኒካል ሙከራዎች ላይ አዲስ የኤችአይቪ/HIV ህክምናዎች ያጠናል ወይም የድሮን ህክምናዎች አሰጣጥ አዳዲስ መንገዶችን ያጠናል።

### 5) ርህራሄ ባለው አቅርቦት

የንግድ ምልክት ብራንድ ስም ያላቸውን መድሃኒቶች የሚያመርቱ የኤችአይቪ/HIV ፋርማቲካል መድሃኒት ኩባንያዎች መዲኬር ላልተፈቀደላቸው ሰዎች (መዲኬር ካርዶች ሳይኖር) 'በርህራሄ ባለው አቅርቦት መርሃ ግብሮች' በኩል ህክምና ሊቀርብላቸው ይችላል።

በማንኛውም መንገድ ህክምና ለመጠቀም ካልቻሉ ታዲያ ለኤችአይቪ/HIV መድሃኒት ርህራሄ ባለው አቅርቦት በኩል ማግኘት ስለመቻልዎ የርስዎን ኤችአይቪ/HIV ሀኪም ማነጋገር አለብዎት። ከPLHIV የሚቀርብ የግለሰብ ማመልከቻ ተቀባይነት አይኖረውም። እርስዎን ወክሎ የገንዘብ እርዳታ ለማመልከት ያለዎትን ሁኔታ ለማስረዳት የ QPP'ን ማነጋገር ይችሉ ይሆናል፤ ወይም በሌላ አማራጭ ደግሞ ለርስዎ የኤችአይቪ/HIV ሀኪም ወይም ለኩዊንስላንድ ኤችአይቪ/HIV ህዝባዊ የጤና ጥበቃ ቡድን በዚህ የሚታይ ድህረገጽ መርበብ: www.tinyurl.com/jqxcn29 ላይ ማነጋገር።

### 6) ለድንገተኛ ችግር የገንዘብ እርዳታ

ከዚህ በላይ ያሉትን ሁሉንም አማራጮች ከጨረሱ ወይም የገቢ ምንጭ ስለሌለዎት ወይም መጠነኛ ገቢ ካለዎት እና ሁሉን ያካተተ መድሃኒት ለመግዛት አቅም ስለማይኖርዎ ለ**ኩዊንስላንድ ኤችአይቪ/ HIV ለድንገተኛ ህክምና የገንዘብ እርዳታ** ለማመልከት ሊፈቀድልዎት ይችላል። በዚህ የገንዘብ እርዳታ ማድረግ የሚቻል:

- a. ለ 3 ወራት ሁሉን ያካተት መድሃኒት መግዣ።
- b. ለኤችአይቪ/HIV ህክምና እንክብካቤ: እስከ ሁለት ክሊኒካዊ መማከርቶች

**እባክዎ ለሚከተለው ያነጋግሩ**
**Queensland Positive People (QPP)**
**በድህረገጽ: info@qpp.org.au**
**ወይም ስለ የገንዘብ እርዳታ ከእኛ ህክምናና ድጋፍ አቅርቦት (TSF) ጋር በስልክ 1800 636 241 አድርጎ ማነጋገር።**